**Montgomery County Fire and Rescue Service**

**Community Risk Reduction** • www.mcfrs.org/mcsafe • X @mcfrs

**የልብስ ማድረቂያ ማሽን ደህንነት**

ልብስ ማጠብ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎ  ውስጥ የሚካተት ሊሆን ይችላል።  ነገር ግን የልብስ ማድረቂያ ማሽንዎን መንከባከብ ለቤትዎ ደህንነት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ያውቃሉ? በጥቂት ቀላል የደህንነት ምክሮች የልብስ ማድረቂያ ማሽን እሳት እንዳይከሰት መከላከል ይችላሉ።

- ማድረቂያ ማሽንዎ በባለሙያ እንዲገጠም እና እንዲታደስ ያድርጉ።
- የማድረቂያ ማሽኑን ያለ ብናኝ (lint) ማጣሪያ አይጠቀሙ።
- ከእያንዳንዱ የልብስ ማድረቂያ ጊዜ በፊት ወይም በኋላ የብናኝ (lint) ማጣሪያውን ማፅዳትዎን ያረጋግጡ። የብናኝ ማጣሪያው ዙሪያ የተሰበሰበውን ብናኝ ያስወግዱ/ያጽዱ።
- ትክክለኛ የአየር ፍሰት እና የማድረቂያ ጊዜን ለመጠበቅ እንዲቻል ከብረት የተሰራ ጠንካራ ወይም ተጣጣፊ የአየር ማስወጫ  ጥቅም ላይ መዋል አለበት።
- የአየር ማስወጫ ቱቦው ያልተደፈነ መሆኑን እና ማድረቂያው በሚሰራበት ጊዜ የውጪው የአየር ማስወጫ ክፍት መሆኑን ያረጋግጡ። በዓመት አንድ ወይም በተደጋጋሚ ጊዜ ልብሶችዎን ለማድረቅ ከመደበኛው ጊዜ በላይ የሚወስድ መሆኑን ካስተዋሉ ከአየር ማስወጫ ቱቦ ውስጥ ብናኝ (lint) እንዳይኖር ያጽዱት ወይም የብናኝ (lint) ማስወገጃ አገልግሎት በሚሰጡ ባለሙያዎች በኩል እንዲጸዳ ያድርጉ።
- የማድረቂያ ማሽኖቹን በጥሩ ሁኔታ ይያዙ። በጋዝ የሚሰራ የልብስ ማድረቂያ ማሽን ከሆነ የጋዝ መስመሩ እና የተገናኘበት ቦታ ያልተበላሸ እና ፍሳሽ የሌለው መሆኑን ለማረጋገጥ በባለሙያዎች መፈተሽ አለባቸው።
- ትክክለኛው የሶኬት መሰኪያ ጥቅም ላይ መዋሉን እና ማሽኑ በትክክል መገናኘቱን ያረጋግጡ።
- የፋብሪካውን የአሠራር መመሪያዎች ይከተሉ እና ማድረቂያው ከሚችለው  መጠን በላይ አያስገቡ።
- ከቤት ሲወጡ  ወይም ወደ መኝታ ሲሄዱ የማድረቅያ ማሽኑን ያጥፉ።

**ያስታውሱ…**

የማድረቂያ ማሽኖች  ወለል ላይ በትክክል መቀመጥ አለባቸው።

የውጪውን የአየር ማስወጫ ፍላፕ በበረዶ ያልተሸፈነ መሆኑን ለማረጋገጥ ይመልከቱ።

የማድረቂያ ማሽንዎ አካባቢን ሊቃጠሉ ከሚችሉ ነገሮች ለምሳሌ ካርቶኖች ፣ የጽዳት እቃዎች እና አልባሳት ወዘተ ነጻ ያድርጉ።

ተቀጣጣይ የሆኑ ንጥረ ነገሮች ማለትም እንደ ቤንዚን፣ የቀለም ማቅጠኛ ወይም መሰል ንጥረ ነገሮችን የነኩ ልብሶች በማሽን ከመታጠባቸው እና ከመድረቃቸው በፊት እንዲደርቁ መቀመጥ አለባቸው ፤ ከደረቁ በኃላ እንደተለመደው በማሽኑ ታጥበው ሊደርቁ ይችላሉ።

**ልብ ይበሉ**

በቤት ውስጥ የሚገኙ የልብስ ማድረቂያ ማሽኖች እሳት መነሳት ዋነኛው መንስኤ ማሽኖቹን አለማጽዳት ነው።

ለነጻ የቤት ደህንነት ፍተሻ ወደ 311 ይደውሉ

www.mcfrs.org/mcsafe